# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 185 ህዳር 21 2004 ገጽ 1


**ግንቦት 7: የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አሁን የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ላይ እየተሞከረ ያለው አደገኛ ጣልቃ ገብነትን አጥብቆ ይቃወማል። አደጋው በእስልምና ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሃይማኖቶችም ላይ ነው፤ በእስልምና ላይ እየተሞከረ ያለው ከተሳካ ነገ ወደሌሎቹም ይዛመታል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ በመላው አገሪቱ የፍርሃት ድባብ ለማስፈን ሲል በውሸት አቀነባብሮ በቴሌቪዥን ያስተላለፈው የአኬልዳማ ድራማ ብዙዎችን እያነጋገረ መሆኑ ተገለጸ

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ እየፈጸመ ያለውን የአገር ሃብት ዘረፋና የስልጣን ብልግና በመቃወም የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ለማጥፋት ሲባል በ3 ተከታታይ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ተቀነባብሮ የተላለፈው የፈጠራ ድራማ ህዝብን በሰፊው እያነጋገረ መሆኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው የህዝብ አስተያየት ገለጸ።

አኬልዳማ የሚል መጠሪያ የተሰጠው ድራማ በክፍል አንድና ሁለት ኦነግና ኦብነግ ፈጽመውታል የተባለውን ግዲያዎች ቅንብር ያስተላለፈ ሲሆን በክፍል ሶስት ደግሞ ግንቦት7 በአገር ውስጥ እየዘረጋው ነው የተባለውን ድርጅታዊ መዋቅር ምንነት ለማሳየት የሞከረ ነበር።

በአዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች ከሚኖሩት የህብረተሰብ ክፍሎች በዘጋቢያችን የተሰባብሰቡ የህዝብ አስተያየቶች እንዳመለከቱት፤ ወያኔ የራሱን የአገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም ድህረ ምርጫ 97 በአዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች ባሰማራው የአጋዚ ጦር በጠራራ ጸሃይ የጨፈጨፋቸው ሰላማዊ ዜጎች ትውስታ ገና ከህዝብ አዕምሮ ሳይፋቅ በማን፤ መቼና የት ቦታ እንደተፈጸመ በውል ያልተገለጹ የህጻናት ግዲያዎች በኦነግና ኦብነግ ተፈጽመዋል ተብለው በምስል ቅንብር በቴለቪዥን መቅረቡ አገዛዙ የገባበትን የስነልቦና ኪሳራና ውድቀት ማሳየት የቻለ ነው።

የአጋዚ ጦር የሰጠው ማስፈራሪያ ምንንነት በደንብ ሳይገባው ይጫወትበት የነበረውን የጨርቅ ኳስ ሩጦ ለመውሰድ ሲንደረደር የነበረውን የ10 አመቱን ህጻን ነቢዩን ጨምሮ ወደትምህርት ቤት ይሄዱ የነበሩትን 13ና 14 አመት ታዳጊዎች ባንክ ሊዘርፉ ነው በሚል የፈጠራ ወንጀል ጭንቅላታቸውን በጥይት አስበጭቶ ያስገደለው መለስ ዜናዊ፤ ለዜጎች ህየወት ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት ያሰራው የአኬልዳማ ቅንበር የታሰበለትን አላማ ለማሳካት ያልቻለ የተለመደ የወያኔ ቅጥፈት ተደርጎ መወሰዱን ዘጋቢያችን አረጋግጦአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ ጉዳይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱና የተለያዩ መጽሃፎችን የጻፉ ታዋቂው የፖለቲካና ታሪክ ምሁር ጆን ማርካኪስ ፣ ህወሀት መራሹ አገዛዝ ከደርግና የሀይለስላሴ ስርአቶች ውድቀት ለመማር ባለመቻሉ፣ እሱም በተራው ወደ ውደቀት እየተጓዘ ነው አሉ

ለረጅም ጊዜ በአገራችን ፖለቲካ ሰፊ ጥናት ያካሄዱት ጆን ማርካኪስ "ኢትዮጵያ፣ ዘ ላስት ቱ ፍሮንቲየርስ" የሚለውን አዲሱን መጽሀፋቸውን ለማስተዋወቅ በለንደን ቻትሀም ሀውስ በተገኙበት ወቅት ህወሃት መራሹ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስልጣን በበቂና ተጨባጭ በሆነ መልኩ ወደ ክልሎችና ወደ ወረዳዎች ለማስተላለፍ ባለመቻሉ፣ የመፈረካከስ አደጋ ተጋርጦበታል ብለዋል።

በዚህ ስነሥርዓት ላይ ተመሳሳይ ንግግር ያደረጉት ሌላው ታዋቂ ምሁር ፕሮፌሰር ክርስቶፈር ክላፋም የኢትዮጵያ መንግሥት እጅግ አሳዛኝ የሆነ መንግስት ነው ብለውታል።

ኢትዮጵያ በውስጥና በአካባቢው ተጽኖ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አገደኛ ሁኔታ ውስጥ እንደምትገኝ የገለጡት ምሁሩ፣ ህወሀት እጅግ ፈላጭ ቆራጭ በሆነ መንገድ በስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያደርገው ጥረት፣ የኢትዮጵያን መጻኢ እድል አደጋ ላይ ጥሎታል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

ሁለቱ ምሁራን ያቀረቡት ጽሁፍ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት አክብሬያለው፣ ፌደራሊዝምን ተግባራዊ አደርጋለሁ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ከመቼውም ጊዜ በላይ አስጠብቄያለሁ ለሚለው ወያኔ ኢህአዴግ፣ ትልቅ የዲፕሎማሲያዊ ውድቀት እንደሚያስከትልበት አስተያየቶች ቀርበዋል።

ፕሮፌሰር ክላፋም በእንግሊዞች ፖለቲከኞች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ካላቸው ምሁራን አንዱ ናቸው።

# ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በጀርመን የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በሰላማዊ ሰልፍ ጠየቁ

እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ከትናንትና ወዲያ ማክሰኞ ኖቨምበር 29 ቀን በፍራንክፈርት ጀርመን የተቃውሞ ሰልፉን ያካሄዱት ኢትዮጵያዊያን፤ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገራችን ውስጥ እየፈጸመ ያለው ገደብ የለሽ ግፍና ሰቆቃ እንዲቆም ለመጠየቅ መሆኑን የሰልፉ አስተባባሪዎች መናገራቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው በላከልን ዜና ገልጾአል።

የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ለመግታት በፓርቲ መሪዎች፤ በአባላቶቻቸውና ነጻ ጋዘጤኞች ላይ እየተወሰደ ያለውን እስርና እንግልት አጥብቀን እንቃወመዋለን ያሉት ሰልፈኞች፤ ከጀርመን ግብር ከፋይ ህዝብ ተሰብሰቦ በሚሰጥ ገንዘብ ወያኔ እየፈጸመ ያለውን ወንጀል የጀርመን መንግሥትና ህዝብ እንዲገነዘብ ለማስቻል በጀርመንኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ደብዳቤ ቅጂ ለብዙ ሺ ህዝብ በትነዋል።

መለስ ዜናዊ ለፍርድ ይቅረብ፤ መለስ ዜናዊ ነፈሰ ገዳይ ነው፤ መለስ ዜናዊ ሽብርተኛ ነው፤ ሞት ለመለስ ዜናዊ፤ ሞት ለወያኔ መሪዎች፣ የታሰሩት ንጹሀን ዜጎች ይለቀቁ፣ የመሬት ሽንሽናው ይቁም፣ ጀርመን አምባገነኖችን አትርዷ የሚሉና ሌሎችም በርካታ መፈክሮች በእለቱ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተስተጋብተዋል።

ኢትዮጵያኑ ከዚህ ቀደም በኑረምበርግ ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፍ ያካሄዱ ሲሆን፣ በሚቀጥሉት ሳምንታትም በዋና ከተማዋ በርሊን ተመሳሳይ ሰልፍ ለማድረግ ዕቅድ እንዳላቸው የደረሰን ዜና ያመለክታል።

የመለስ አገዛዝ ሰለማዊ ዜጎችንና የነጻነት ታጋዮችን አንዴ በአሸባሪ ሌላ ጊዜ በአገር ክዳት ወንጀል ስም ማሰሩ አለማቀፍ ውግዝት እያስከተለበት ነው። የአለማቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅት ሲፒጄ ፣ ሂውማን ራይትስ ወች እና አምነስቲ ኢንተርናሽናል የመለስ አገዛዝ ሀሳብን በጉልበት ለማፈን የሚደረገውን ሙከራ መቃወማቸው ይታወሳል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ባለፈው እሁድ የተካሄደው የዘንድሮው ታላቁ ሩጫ እንደወትሮው የብሶት መግለጫ ሆኖ ማለፉ ተዘገበ

ባለፈው እሁድ ለ11ኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተካሄደው ታላቁ ሩጫ የተሳተፉ ዜጎች፤ ወያኔ መራሹ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በአገራችን ውስጥ እያሰፈነ ያለውን ኢፍትሃዊነትና አፈና የሚያወግዝ መፈክሮችን ሲያሰሙ እንደዋሉ የግንቦት 7 ዜጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዜና አስታወቀ።

በዚይ የህዝብ ብሶት ሲስተጋባበት በዋለው የሩጫ ውድድር የተሳተፉት፤ ከምዝገባው ጀምሮ በተቻለ መጠን ለወያኔ ፖለቲካ ወገንተኝነት ያላቸው እንዲሆኑ በአዘጋጆች በኩል ጀምሮ አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ እንደነበር የጠቀሰው ዘጋቢያችን፤ በአገራችን የሰፈነው የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ያልዳሰሱት የህብረተሰብ ክፍል ባለመኖሩ በውድድሩ ላይ በየአመቱ ሲስተጋቡ የቆዩትን እንዲህ አይነቱን ብሶቶች ዳግም እንዳይሰማ ለማድረግ ተደርጎ የነበረው ሙከራ ሳይሳካ ቀርቶአል ብሎአል።

ታላቁ ሩጫ በድህረምርጫ 97 የታሰሩት የቅንጅት መሪዎች፤ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጉዳይ በህብረተሰቡ ውስጥ የቀሰቀሰውን ተቃውሞና ጸረ ወያኔ ስሜት መግለጫ መሆኑ ተደጋግሞ በመታየቱ ፤ ብዙ አፍቃሪ የፈጠረውን ይህንን ታላቅ ሩጫ ከማስቀረት መነሻው ከመስቀል አደባባይ ሆኖ አገዛዙ ቁንጮ በከተመበት ቤተመንግሥት በኩል ወደ አራት ኪሎ ያልፍ የነበረውን መስመር በመዘጋት ካለፈው አመት ጀምሮ ከመስቀል አደባባይ በሜክስኮ አድርጎ ወደ ጎተራ አቅጣጫ ደርሶ መልስ እንዲሆን ተወስኖአል። ይህም ሆኖ ግን ህዝብ የተሰማውን ብሶት ለማፈን እንዳልተቻለ ባለፈው እሁድ የተካሄደው ሩጫ አረጋግጦአል እንደዘጋቢያችን ሪፖርት።

ቁጥራቸው ከሰላሳ ስድስት ሺህ በላይ ህዝብ ተሳትፎበታል የተባለው የዘንድሮው ታላቁ ሩጫ የወያኔ ፕሮፖጋንዳ መሳሪያ ሆኖ በማገልገል ላይ በሚገኙ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በቀጥታ ይተላለፍ እንደነበረ የዘገበው ዘጋቢያችን፤ ሩጫው ከተጀመረ ጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የተቃውሞ መፈክሮች መስተጋባት እንደጀመሩና እቤቱ ሆኖ ፕሮግራሙን ይከታተል የነበረው ህዝብ ፏጮች ጣቶቻቸውን እየቀሰሩ "ሌባ ሌባ ኢህአደግ ሌባ" እያሉ ያደርጉትን የነበረውን ጩሄት ይመለከት እንደነበር ገልጾአል። ሆኖም አገዛዙን የሚያወግዙ መፈክሮች እየተበራከቱ በመምጣታቸው በኢትዮጵያዊያን ግብር ከፋይ ሥም እየተዳደረ መልሶ ህዝብ ለማፈኛ አገልግሎት ላይ እየዋለ ባለው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚስልና ድምጽ ውህደቱን በማቋረጥ ድምጽ አልባ የሆነ ምስል በስቱዲዮ ሰራተኞች የድምጽ ቅንብር ለማስተላለፍ እንደተገደደ ለማረጋገጥ ተችሎአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የእምነት ነፃነት፤ የሰብዓዊ መብቶች አካል ነው

በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 18 መሠረት እያንዳንዱ ሰው በግሉም ሆነ በጋራ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተልና የማስተማር፤ ያልፈለገውን ደግሞ የመተው መብት አለው።

እንደሚታወቀው፤ ሰብዓዊ መብቶች እርስ በርሳቸው የተቆራኙ፤ እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ ናቸው። አንዱ የመብት ዓይነት ሲጓደል፤ ሌላውም አብሮ ይጓደላል። ለምላሴ የመናገር መብት ተገፎ እያለ የማምለክ መብት ሊፋፋ አይችልም፤ ወይም ደግሞ ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብት ተጥሶ እያለ የማምለክ መብትን የሚያስከብር ተቋም ሊኖር አይችልም። ለዚህም ነው ሰብዓዊ መብቶች የማይነጣጠሉ ናቸው የሚባለው።

በአገራችን እየተባባሰ የመጣው በእምነት ላይ ያለው ግልጽ አፈና በአጠቃላይ በሰብዓዊ መብቶች ላይ ያለው አፈና አንድ ዓይነተኛ መገለጫ ነው። አገዛዝ በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር የነበረባቸው ተቋማት ሰብዓዊ መብቶችን መርገጫ እንደሚሆኑ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥር ያለችውን አገራችንን ማየት በቂ ነው። በአገዛዙ ሥር ያሉ ፍርድ ቤቶች እየሠሩ ያሉት ምንድነው? ምንድነው "የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን" እየሠራ ያለው? ምንድነው "የሕዝብ እንባ ጠባቂ ኮሚሽን" እየሠራ ያለው? ምንድነው ፓሊስ፣ ምርጫ ቦርድና ፓርላማ እየሠሩ ያሉት? ጥያቄዎቻችንን መቀጠል እንችላለን። ምላሹ ግን አንድ ነው። እነዚህ መሰል ተቋማት በአገዛዝ ሥር ሲወድቁ የሰብዓዊ መብቶች መርገጫ እንጂ ማስከበሪያ ሊሆኑ አይችሉም። በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ውስጥ ደግሞ እነዚህ ተቋማት የአፈና ብቻ ሳይሆን የዘረኝነትም ማስፋፊያ ናቸው።

የአገዛዝ ሥርዓት አፈናውን ባጠናከረ መጠን የመንግሥት ተቋማትን ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ተቋማትንም ጭምር የጭቆናው መሣሪያ ያደርጋቸዋል። ለዚህ ደግሞ ገሃድ ምሳሌ የሃይማኖት ተቋማቶቻችን ናቸው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ በሁሉም ሃይማኖቶች ተቋማት ውስጥ የራሱን ካድሬዎች በመሾም ምዕመናኑን ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ የጀመረው ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእምነት ተቋማት መሪዎች ከእምነት መሠረታዊ መርሆዎች ያፈነገጡ ተግባራትን ሲተገብሩ ማየት እጅግ የተለመደ ነገር እየሆነ መጥቷል።

በእምነቶችና በእምነት ተቋማት ላይ እየደረሰ ያለው በደል ሁሉንም ሃይማኖቶች ያዳረሰ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በእስልምና ሃይማኖትና በሙስሊም ማኅበረ -ሰብ ላይ እየደረሰ ያለው አፈና ግን ከሁሉም የከረረ እና የመረረ ሆኗል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የመጅሊስን አመራር በራሱ ካድሬዎች ከማስያዝ በላይ በዝርዝር ሃይማኖታዊ አስተምህሮት ውስጥ በመግባት አንዱን ጀማ ወዳጅ፤ ሌላኛውን ደግሞ ጠላት እያደረገ ነው።

ዘረኛው አገዛዝ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮችን ከማጋጨት አልፎ በአንድ ሃይማኖትም ውስጥ የተለያዩ ጎራዎች እንዲፈጠሩና እርስ በርሳቸው እንዲጋጩ እያደረገ ነው። ይህ አካሄድ እጅግ ክፋት የተሞላበት ውጤቱም አደገኛ የሆነ ነገር ነው።

ለምንድነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአሁኑ ሰዓት በተለይ በእስልምና ሃይማኖትና በሙስሊም ማኅበረሰብ ላይ ያነጣጠረው? ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የሚከተሉት ሁለቱን ብቻ ማንሳት ይበቃል።

1. መለስ ዜናዊ "ሙስሊም ለፓለቲካ ደንታ የለውም" የሚል የትዕቢት አስተሳሰብ ተቆራኝቶት ቆይቷል። ሆኖም ግን እያለቀ ባለው የአውሮፓውያን ዓመት በሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ እየታዩ ያሉ ለውጦች መለስንና የመለስ ዓይነት ሰዎችን መግቢያ ቀዳዳ አሳጥቷቸዋል። የሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶች ሙስሊም ወገኖቻችን ለፍትህና ለዲሞክራሲ ያላቸውን ጥማት ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነታቸውንም አጉልቶ አሳይቷል። መለስ ዜናዊና ጋሻ ጃግሬዎቹ አሻግረው እያዩት ያለው ሕዝባዊ ማዕበል እንዳይውጣቸው መፍትሄ አድርገው ያቀረቡት ሙስሊሙን መከፋፈል ነው።
2. የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል የከረረ ጥል ለመፍጠር ያልቆፈረው ጉድጓድ የለም። በተለይም ሙስሊሙንና ክርስቲያኑን ማኅበረሰብ ለማቃቃር ብዙ ጥሯል። በሰኔ 2001 በደሴ አርሴማ ቤተክርስቲያን ግንባታ ሰበብ ሆነ ብሎ ያስነሳው ጠብ አንዱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ሆኖም ግን መለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ በፈለጉት መጠን ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች አልተጣሉም። ጊዜዓዊ ግጭቶችም በተከበረው አገራዊ የሽምግልና ባህል እየተፈቱ እርቅ የሚወርድ በመሆኑ መለስ አዲስ እና የከፋ ዘዴ መሸረብ ነበረበት። አዲሱ ዘዴ፣ የእያንዳንዱ ሃይማኖት አማኝ እራሱ ከራሱ ጋር እንዲጣላ ማድረግ ሆነ።

ግንቦት 7: የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አሁን የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ላይ እየተሞከረ ያለው አደገኛ ጣልቃ ገብነትን አጥብቆ ይቃወማል። አደጋው በእስልምና ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሃይማኖቶችም ላይ ነው፤ በእስልምና ላይ እየተሞከረ ያለው ከተሳካ ነገ ወደሌሎቹም ይዛመታል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የአምልኮት ነፃነት ማጣት የሰብዓዊ መብት እጦት መሆኑን ሁላችንም መረዳት ይኖርብናል። መፍትሄም የሚገኘው በተናጠል ሳይሆን በጋራ ነው። ልናስከብረው የሚገባ መብትም ሰብዓዊ መብቶችን በሙሉ ነው።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ተወግዶ ዲሞክራሲያዊ እና ፍትሃዊ ሥርዓት ሳይገነባ ሰብዓዊ መብቶች መከበር የማይችሉ በመሆኑ ትኩረታችን በዋነኛው የጋራ ጠላታችን በሆነው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ላይ መሆን ይኖርበታል።

ሙስሊሙ ወገናችን፣ ሰብዓዊ መብቶች ሳይከበሩ የሃይማኖት ነፃነት ብቻውን መከበር የማይችል መሆኑን ተረድቶ መለስ ዜናዊን ለማስወገድ በምናደርገው የጋራ ትግል በጽናት እንዲቆም ግንቦት 7 ጥሪ ያደርጋል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ሳይወገድ ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር ስለማንችል አንድነታችንን አጠንክረን የነፃነት ትግላችንን እናፋፍም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

.................................................................................................................................................

## ወያኔ በመላው አገሪቱ የፍርሃት ድባብ ለማስፈን ሲል በውሸት አቀነባብሮ በቴሌቪዥን ያስተላለፈው የአኬልዳማ ድራማ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ኦነግ በሚከሰስበት የበደኖ ግዲያ ወቅት ሥልጣን ላይ የነበረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የህዝብ ወገንተኛነት ቢኖረው ኖሮ የተገደሉትን ሰዎች ምስል በፊልም የሚቀርጽ ሃይል በቦታው ከማሰማራት ይልቅ ወንጀሉን ለመከላከል አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድና ተጠያቂዎቹንም ህግ ፊት የማቅረብ ግዴታ ነበረበት የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች፤ ኦነግ በተገንጣይነት ከወያኔ ጋር የነበረው ተመሳሳይ አጀንዳ በሂዴት ተለውጦ ከአንድነት ሃይሎች ጋር መቀራረብ በመጀመሩ በተፈጠረ ድንጋጤና ጭንቀት፤ በአለም አቀፍ የሚዲያ ህግ የተከለከለ አሰቃቂና ዘግናኝ ምስሎችን ለህዝብ እይታ ለማቅረብ ችሎአል ብለዋል።

በአኬልዳማ ክፍል ሶስት የተቀነባበረው ድራማ እንዳመለከተው፤ አገር ውስጥ ተመዝግበው በሰላማዊ የትግል ስልት መንግሥት ለመቀየር የሚንቀሳቀሱ ፓርቲ መሪዎችና አባላት አለአግባብ ከታሰሩ ቦኋላ ለመስከረም 24 ተጠርቶ የነበረው ህጋዊና ሰላማዊው የተቃውሞ ሰልፍ "ነውጥና ሽብር በአገሪቱ ውስጥ ለማነሳሳት የተዘጋጀ" ነው በማለት በዱላና ሌሎች ወያኔያዊ የጥቃት እርምጃ ተገደው እንዲመሰክሩ የተደረገበት መሆኑ ብዙዎችን በማስቆጣት ለትግል እያነሳሳቸው ነው ተብላአል።

ወያኔ ባላሰበው ሰዓትና ጊዜ ሊፈነዳ ይችላል ብሎ የሚፈራው ህዝባዊ አመጽ እንዳይቀሰቀስ ዜጎችን በሙሉ በፍርሃት ቆፈን ውስጥ ለመክተት ተብሎ በተቀነባበረው በዚህ የአከልዳማ ክፍል ሶስት ቅንብር ፤ግንቦት 7 የወያኔን መሪዎች ምን ያህል እረፍት እየነሳው የመጣ ድርጅት እንደሆነ በግልጽ የተመሰከረበት በመሆኑ ፤ የነጻነት ትግሉን ሊመራ የሚችል ፓርቲ ገና ያላገኘ መስሎት በፍርሃትና ተስፋ መቁረጥ አንገቱን ደፍቶ የነበረው ህዝብ እንዲነቃቃና እንዲጽናና አስችሎታል ብሎአል የግንቦት 7 ዘጋቢ መረጃ።

በአኬልዳማ ድራማ ላይ "በግንቦት 7 ታዝዤ ነውጥ ለመቀስቀስ ስንቀሳቀስ ነበር ብሎ" ቃላቸውን እንዲሰጡ ከተደረጉት መካከል በሽብርተኛነት ክስ መዝገብ በ5ተኛ ተራ ቁጥር ተከሳሽ የሆነው ክንፈሚካኤል ደበበ በረደድ (አበበ ቀሲቶ) በትናትናው ዕለት በዋለው የወያኔ ችሎት ፍት ቀርቦ እምነት ክህደት ቃሉን በተጠየቀበት ወቅት "ክቡር ፍርድ ቤት እዚህ የክሥ ቻርጅ ላይ የተዘረዘሩትን ተረታ ተረቶች አልፈጸምኩም፣ ወደፊትም አልፈጽምም፤ መንግሥት የእኛን ብቻ ሳይሆን የፍርድ ቤቱን ክብር ነው ያሳጣው- በፍርድ ቤት ሥራ ጣልቃ እየገባ' በማለት መልሥ እንደሰጠ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

በትናትናው የፍርድ ቤት ውሎ የእመነት ክህደት ቃላቸውን ከተጠየቁት መካከል፡ 1ኛ ተከሳሽ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አንዷለም አራጌ "ይህ በኢትዮጵያ ሠላማዊ ትግልን ለማፈን የተዘጋጀ የውሸት ድሪቶ ነው፤ እኔ ምንም አይነት ወንጀል (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በከፉዎች ምክር ያልሄደ ምስጉን ነው!!

በአገራችን ላይ ክፉ ምክር ሲመከር እነሆ ሁለት አስርተ ዓመታት ተቆጠሩ። አንድ ህዝብ የሌላው ህዝብ ጠላት እንዲሆን ተሰብኳል። በህዝብ መካከል ቋሚ ጥላቻን የሚመሰክሩ ሃውልቶችም ቆመዋል። አገሪቷ የነበራት እሴቶች ሆን ተብለው በጥናት ተዘምቶባቸዋል። የአገሪቷ ህግ በአንድ ክፉ ጣኦት ስሜት ተተክቶ ፍትህ በመጥፋቱ ዜጎች ለእስራት፤ ለስደትና ለውርደት ተዳርገዋል። ውርደቱ ወደ ክፉ ሮሮ በመሸጋገሩ ዜጎች እያለቀሱ ነው።መጽሃፈ ምሳሌ “ኃጥአን በሰለጠኑ ግዜ ህዝብ ያልቀሳል” ያለው በአገራችን እውነተኛ ታሪክ ሆኖ እየታየ ነው። የመምህር የኔሰው ገብሬ በራሱ ላይ ላምባ አርከፍክፎ መቃጠልም የዚህ ውጤት ነው።

መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ ስቃዩ በዝቶበት ራሱን መሰዋእት ያደረገውን ምስጉን መምህር የአእምሮ ህመምተኛ ነው ብለዋል። የዋካ ከተማ ሃኪሞችንም በዚህ ውሸታቸው እንዲተባበሯቸውና ከክፉ ምክራቸው ጋር እንዲቆሙላቸው ለማድረግ እየሞከሩ ነው። እነመለስ ዜናዊ የገዛ ውሸታቸውን አምነው ዜጎችም እንዲዋሹላቸው ለማድረግ ከላይ እግዜርን ከታች ሰውን የሚያፍሩ አይደሉም። ባለንበት ወቅት ከእነዚህ ዘረኞችና የህዝብ ጠላቶች ጋር አለመቆም በምክራቸውም አለመሄድ ትልቅ መስዋእትነት የሚጠይቅ ተግባር ነው። የዋካ ከተማ ሃኪሞች መምህር የኔሰው ገብሬ የሞተለትን ዓላማ ለመረዳት እዝነ ልቦናቸው መለስ ዜናዊ በሚወረውረው ፍርፋሪ የተያዘ አይደለም። ያዩትን ለመመስከር የሞራልም ሆነ ህጋዊ ግዴታ አለባቸውና ከዘረኞችና ከህዝብ ጠላቶች የሚሰነዘርባቸውን ዛቻና ማስፈራሪያ ችላ በማለት እውነቱን መናገር ይጠበቅባቸዋል። እውነቱም መምህር የኔሰው ገብሬ የአእምሮ ህመምተኛ ሳይሆን ሙሉ ጤነኛ የሆነና የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ መሆኑ ነው።

የኔሰው ገብሬ የእኛ ሙሃመድ ቡዛዚ ነው።በመለስ ዜናዊ የተዘረጋው ዘረኛ አገዛዝ የመረረው፤መከራው በዝቶ በሮሮ ውስጥ መኖር የሰለቸው ነጻነት ፈላጊ ክቡር ዜጋ ነው። ይህን ለነጻነት ራሱን መስዋእት አድርጎ ያቀረበውን ወጣት መምህር የአእምሮ ህመምተኛ ነበር ብለው የጻፉ እጆችን በጥንቃቄ እየተመለከትን ነው። ዜናውን ያወጁትን ይዘናቸዋል። ዋካ ድረስ ገስግሰው ሂደው የነጻነት አርበኛውን ታሪክ የሚያጠፋ ጉድፍ ዘገባ ያዘጋጁትንና ዜናውን ያቀናበሩት እንማን እንደሆኑ አውቀናቸዋል። እንዲህ ያለ ነውር ተግባርን ለእንጀራየ ብየ ሰራሁ ማለት ከምንም የሚያድን ተግባር እንዳልሆነ አበክረን ማሳሰብ እንወዳለን። የመለስ ዘረኛና ዘራፊ ስርዓት ንፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ የሚሆንበት ግዜ ሩቅ አይደለም። ያን ግዜ እውነት ትነገራለች። እውነት በተነገርች ግዜ በአፋቸው እውነት ተፈልጎ የሚገኝባቸው ዜጎች ይመሰገናሉ። እውነት ተፈልጋ ስትታጣ ለእንጀራየ ብየ ስዋሽ ኖርኩ የሚሉትን ግን እግዜር እላይ ከሰማይ ሰውም ከዚህ ከምድር ይታዘባቸዋል። ያን ግዜ የሞራልም ሆነ የህግ ተጠያቂነትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ነውር ተግባራት ሁሉ ይገለጣሉ።

በአገሪቷ ላይ ክፉ ጣኦት ነግሶ እንዲህ ወገንን በሚያሰቃይበት ወቅት የስቃዩን ምንጭ ጣኦት አለመዋጋት ነውር ነው። ክፉ አድራጊዎችን አለመቃወም ነውር ነው። ሃሰት የሚናገሩትን ዝም ማለት ነውር ነው። ዜጎችን የሚያሳድዱትን ተው አለማለት ነውር ነው። ጉሮሮአቸው እንደተከፈተ መቃብር ዜጎችን ሲውጥ እያዩ ዝም ማለትም ነውር ነው።

የመለስ ዜናዊ ጉሮሮ እንደተከፈተ መቃብር ዜጎችን እየዋጠ የአገራችን ስቃይና መከራዋን አብዝቷል። ይህን ስቃይና መከራ የሆነ ግለሰብ ከዚያች አገር ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ተነቅሎ ስም አጠራሩ እንዳይታወቅ ለማድረግ ግንቦት ሰባት የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። ዜጎችም በያሉበት ሁነው በሚችሉት ሁሉ ይህን የእኩይ ተግባራት ምንጭ የሆነውን ግለሰብና ቡድኑን መታገል ወቅቱ የሚጠይቀው ትክክለኛ ተግባር ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## ለአባይ ግድብ የሚሰበሰበው ገንዘብ አባይን ይገድባል ተብሎ ሳይሆን ህዝብን ቁጠባ ለማስተማር ነው ሲል በሰሜን አሜሪካ የወያኔ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ግርማ ብሩ አስታወቀ

ግርማ ብሩ ይህንን ያስታወቀው በፈረንጆች አቆጣጠር ያለፈው ሳምንት ኖቨምበር 20 ቀን በአትላንታ ከተማ አፍቃሪ ወያኔዎችን የሚላኒዬም ግድብ ብሎ ለተሰየመው ማደናገሪያ ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጡና ዲያስፖራውን በጥቅማጥቅም ለመያዝ በተረቀቀው አዋጅ ላይ ለመነጋገር ጠርቶአቸው በነበረው ስብሰባ ላይ ነው።

"መንግሥታችን የህዳሴ ግድብ ብሎ የሰየመውን ይህንን ታሪካዊ ግድብ ለመገደብ ሲነሳ፤ ከናንተ ከዲያስፖራው ህብረተሰብ ወይም አገር ቤት ካለው ህዝብ በሚሰበሰብ ገንዘብ ይከናወናል የሚል ቅዥት /Illusion/ ኖሮት ሳይሆን ያገኘውን ሁሉ ወዲያው በማባከን ባህሉ የሚታወቀውን ህዝብ ቁጠባ ለማስተማር ተብሎ ነው" ያለው ግርማ ብሩ፤ የወያኔ ዘረኛ መዋቅር በፈጠረው ሃብት ዘረፋና ሙስና በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ የድህነት አረንቋ ውስጥ ተጥሎ የዕለት ጉርሱን እንኳ መሸፈን የተሳነውን ህዝብ "የቁጠባ ባህል የሌለው" ያገኘውን ሁሉ አባካኝ በማለት ተሳልቆበታል።

ኖቨምብር 20 በአትላንታ ከተማ የተደረገው የወያኔ ስብሰባ ቀደም ሲል ከወር በፊት እንደፈረንጆች አቆጣጠር ኦክቶበር 2 ሊካሄድ ታቅዶ እንደነበር የጠቀሰው ዘጋቢያችን ፤ ለአፍቃሪ ወያኔዎች ብቻ ተበትኖ የነበረው የስብሰባ ጥሪ በጆርጂያ ስቴት የኢትዮጵያዊያን አሜሪካን የጋራ መድረክ እጅ በመግባቱ፤ አገራችን ውስጥ ዜጎችን በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት ብቻ የሚያስር፤ የሚገድልና የሚያሸብር ወንጀለኛ አገዛዝ ፤ ነጻነት በሰፈነበት አገር ተሰደው የሚኖሩትን በመከፋፈል የድጋፍ መሠረት መጣል የለበትም የሚል ተቃውሞ ለከተማው አስተዳደር ባለሥልጣናት በማስገባቱ ለስብሰባ ተከራይተውት የነበረው አዳራሽ እንዲሰረዝ መደረጉን ገልጾአል።

ወያኔ በዘረፋ ከሚያገኘው የአገር ሃብት ትናንሽ ጥቅማጥቅሞች የሚወረወርላቸው ሆዳሞችና ባንዳዎች ሌላ አዳራሽ ፈልገው ስብሰባውን በሌላ ቀን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገው የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያዊያን አሜሪካን ፎረም ባደረገው ተደጋጋሚ ተቃውሞ እዳራሽ የሚያከራይ በመጥፋቱ ከ7 ሳምንታት ቦኋላ ደረጃው እጅግ በወርደና ከአሁን ቀደም በስብሰባ አዳራሽነት አገልግሎት ላይ ውሎ በማይታወቅ የአንድ የግለሰብ ንግድ ድርጅት ውስጥ ሊካሄድ እንደተገደደ የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

ወያኔ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ የህወሃት ተለጣፊ በመሆን የተለያዩ የሹመት እርከኖች ላይ ሲፈራረቅ የኖረው ግርማ ብሩና መለስ ዜናዊ የዲያስፖራውን ህብረተሰብ ለመከፋፈል የነደፈውን ዕቅድ ለማስተገበር አድስ በተከፈተው የኮሚኒቲ ጉዳይ በሃላፊነት የተመደበው ሙሉዬ ታረቀኝ በመሩት የአትላንታ ስብሰባ ቁጥራቸው 100 የማይበልጥ አፍቃሬ ወያኔና ስግብግብ ጥቅም ፈላጊ ሰዎች መሳተፋቸው ታውቆአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛአ በአገራችንና በህዝባችን ላይ ሲፈጽም የኖረውን ወንጀል አይቶ እንዳላየ በመምሰል ለቤት መስሪያ የሚሆን የከተማ ቦታና ኮንዶሚኒዬም ፍለጋ ወያኔ በሚጠርው ስብሰባ ላይ ደፋ ቀና ሲል የኖሩ አንዳንድ የስብሰባው ተካፋዮች፤ ባለፈው ወር በወጣው አዲሱ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅና አለአገባብ እየተጣለ ባለው የግብር ክፊያ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲያሰሙ አንደነበር ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

አንባቢያን ስለ አድሱ የከተማ ቦታ አዋጅ፤ ስለሙስናና ወያኔ የዲያስፖራውን ህብረተሰብ ለመያዝ ያወጣቸውን ስትራቴጂ በሚመለከት በስበብሰባው ላይ የተነሱትን ጥያቄዎችና መልሶች ዘጋቢያችን በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ተከታትሎታል በሚቀጥለው እትም ይዘንላችሁ እንቀርባለን።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሽብርተኝነት የከሰሳቸው 24 ሰዎች ጉዳይ በትናንትናው ዕለት በፍርድ ቤት ተብዬው የወያኔ ካድሬዎች መድረክ ላይ ሲታይ ዋለ።

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በ”ሽብርተኝነት‘ ከወነጀላቸው 24 የፖለቲካ ፓርቲ የአመራር አባላት፣ ጋዜጠኞች እና ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያዊያን መካከል ሀገር ውስጥ በእሥር ላይ በሚገኙት ስምንት ተከሳሾች ላይ በዐቃቤ- ሕግ ተሸሻለ የተባለውን የክስ ቻርጅ በትናትናው ዕለት አቀረበ፡፡ ይህ ተሸሻለ የተባለው የክስ ቻርጅ የቀድሞው አዲስ ነገር ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር እና ዋና አዘጋጅ የሆኑት ዐብይ ተክለማርያምና መስፍን ነጋሽን አያካትትም ተብሏል።

እነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ጽጌ የተካተቱበት ከተከሳሽ ተራ ቁጥር 9 እስከ 24 ያሉት በውጭ አገራት የሚገኙት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ለህዳር 27 ቀን 2004 ዓ.ም ጊዜ ቀጠሮ እንደያዘላቸው ፍርድ ቤቱ ገልፆል።

ዐቃቤ-ሕግ ተብዬው የፌዴራል ፖሊስ በእስር ላይ ባዋላቸው ከተከሳሽ ተራ ቁጥር 1 እስከ 8 ድረስ ያሉት ተከሳሾች ላይ አሻሻልኩ ያለውን ክሥ 1 እና ክስ 4 ከሌሎች ክሶች ጋር አንድ ላይ በ14 ገጽ ያቀረበ ሲሆን፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሦስተኛ ወንጀል ችሎት ክሱን ለተከሳሾች በንባብ አሰምቷል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ለአባይ ግድብ የሚሰበሰበው ገንዘብ አባይን ይገድባል ተብሎ

. . . (ከገፅ 3 የዞረ)

የተከሳሽ ጠበቆች አቶ ደርበው ተመስገን እና አቶ ሣሙኤል አባተ በተሻሻለው አራተኛው ክስ (አሸባሪን በመተባበር) ላይ ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለጹ ሲሆን በአንደኛው (ከአሸባሪዎች ጋር ህብረት በመፍጠር) በሚለው ክስ ላይ ግን ዐቃቤ- ሕግ የጸረ- ሽብር አዋጁን አንቀጽ 3 ከንዑስ አንቀጽ 1- 4 በመጥቀሱ ይህም ህግ በቅደም ተከተል በሽብርተኝነት ተግባር ሰው መግደልን፣ የሕብረተሰብን ደህንነት አደጋ ላይ መጣልን፣ እገታና ጠለፋን፣ በሽብርተኘነት ተግባር በንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ ማድረስን ስለሚጠቅስ እና በተጨባጭ በዐቃቤ- ሕግ የክስ ቻርጅ ላይ ምንም ዓይነት ይህን መሰል የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ እና ማን ምን ዓይነት ወንጀል እንደፈጸመ የሚያመላክት ዝርዝር ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ በድጋሚ የመንግሥትን ባለሥልጣናት ለመግደል፣ ባንኮችን ለመዝረፍና ህብረተሰቡን ለማሸበር የሚል ጨምረውበት እንዳለ የበፊቱ መቅረቡን ተቃውመዋል።

ዐቃቤ- ሕግ በበኩሉ እኛ ክሱን ያቀረብነው ሰው መግደል፣ ንብረት ማውደም ብለን ሳይሆን እነዚህን የወንጀል ተግባራት ለመፈጸም፣ ባለሥልጣናትን ለመግደልና ባንኮችን ለመዝረፍ እና ዜጎች እንዲሸበሩ ማደምና ማሴር በሚል ነው፣ ይህ የተፈጸመ ያለቀ ድርጊት አይደለም ነገር ግን ይህን ለመፈጸም የሥራ ክፍፍል ነው ያደረጉት በማለት ሊሻሻል የሚገባው ክስ አይደለም እላለሁ ብሏል።

ፍርድ ቤቱ አራተኛው ክሥ ተቃውሞ እንዳልቀረበበት በመጥቀስ ያሳለፈው ሲሆን በአንደኛው ክሥ ላይ ግን የተከሳሽ ጠበቆች ተቃውሞ ቢያቀርቡበትም የዐቃቤ- ሕግ የክሥ ዝርዝር በጸረ-ሽብር አዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1- 6 ያለውን ነጥቦች ስንመለከት ክሱ ከቀረበበት የወንጀል ድርጊቶች- ማቀድን፣ ማሴርን፣ መዘጋጀትን የሚመለከት ስለሆነ የተከላካይ ጠበቆች ተቃውሞን ውድቅ አድርገነዋል ሲል ብይን ሰጥቷል።

ፍርድ ቤቱ ወዲያው የተከሳሾችን የእምነት ክህደት ቃል ወደ ማድመጡ የገባ ሲሆን ተከሳሾች አቤቱታችን ይደመጥ ሲሉ ባቀረቡት ሃሳብ ላይ ፍርድ ቤቱ በጽሑፍ አሳውቁ ዛሬ ይሄን አላደምጥም በማለቱ ተነታርከዋል።

ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ- ሕግ ክሥን በተመለከተ የእምነት ክህደት ቃሉን የጠየቀው 1ኛ ተከሳሽ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አንዷለም አራጌ "ይህ በኢትዮጵያ ሠላማዊ ትግልን ለማፈን የተዘጋጀ የውሸት ድሪቶ ነው፤ እኔ ምንም አይነት ወንጀል አልፈጸምኩም...' ሲል ፍርድ ቤቱ በመሐል ገብቶ ዛሬ ሌላ ነገር ለመስማት ዝግጁ አይደለሁም፣ አሁን መናገር የምትችሉት ወንጀሉን ፈጽማችኋል ወይስ አልፈጸማችሁም በቃ! ሲሉ አቶ አንዷለም "ይገርማል እኔ ከዚህ በፊትም ፍርድ ቤት ቀርቤ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ይህ ፍርድ ቤት ለእኛ ፍትህ ለመስጠት የቆመ አያስመስለውም፤ የገጠመንን ኢፍትሃዊነት በተናገርን ቁጥር በጽሑፍ አቅርቡ እየተባልን አድማጭ አጥተን እንገላታለን፣ መንግሥት እኛን በእሥር ላይ አድርጎ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አኬልዳማ በሚል በሦስት ክፍል ፕሮግራም የሥም ማጥፋት ዘመቻ እያካሄደብን ይገኛል።' ብሏል።

ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል ናትናኤል መኮንን "በሠላማዊ መንገድ መታገል ወንጀል ከሆነ አዎን ፈጽሜያለሁ፣ እንጂ የተባለውን የመንግሥት ድርሰት ግን አልፈጸምኩም፡፡' ያለ ሲሆን ሌሎች ተከሳሾች የተባለውን ወንጀል አልፈጸምኩም እያሉ የመለሱ ሲሆን 5ተኛ ተከሳሽ ክንፈሚካኤል ደበበ በረደድ (አበበ ቀሲቶ) በበኩሉ "ክቡር ፍርድ ቤት እዚህ የክሥ ቻርጅ ላይ የተዘረዘሩትን ተረታ ተረቶች አልፈጸምኩም፣ ወደፊትም አልፈጽምም፤ መንግሥት የእኛን ብቻ ሳይሆን የፍርድ ቤቱን ክብር ነው ያሳጣው - በፍርድ ቤት ሥራ ጣልቃ እየገባ' በማለት መልሥ ሰጥቷል።

ፍርድ ቤቱ ተከሳሾችን ክሱን ድርጊቱን ፈጽሜያለሁ ወይም አልፈጸምኩም ከሚል መልሥ በቀር ምንም እንዳይናገሩ ከገሰጸ በኋላ ዐቃቤ- ሕግ-ን ተከሳሾች ወንጀሉን አልፈጸምኩም ብለዋል ምን ትላለህ በሚል ላቀረበው ጥያቄ ዐቃቤ- ሕግ ምንም እንኳ ተከሳሾች ክሱን ባይቀበሉትም በክሥ ማመልከቻ ዝርዝር ላይ ያቀረብነው እንዲታይልን ቀጠሮ እንዲሰጠን እንጠይቃለን ብሏል።

ፍርድ ቤቱም በውጭ አገራት ለሚገኙት ተከሳሾች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ መሠረት ህዳር 27 ቀን 2004 ዓ.ም እንዲቀርቡ ቀጠሮ መያዙን አስታውቆ፣ በሀገር ውስጥ እሥር ቤት ለሚገኙት ስምንት ተከሳሾች ደግሞ ታህሳስ 16 ቀን 2004 ዓ.ም ተለዋጭ ጊዜ ቀጠሮ ሰጥቶ ችሎቱ ተበትኗል፡፡

የመለስ አገዛዝ አኬልዳማ ብሎ የሰራው እጅና እግር የሌለው የፈጠራ እንቶ ፈንቶ ድራማ፣ አገዛዙ በምን ያክል ደረጃ መዝቀጡንና እንደ መንግስትነት እንድናዬው ሳይሆን፣ ተራ ዱርዬም ከሚያስበው በታች የሚያስቡ ሰዎች ይህችን ታላቅ አገር እየገዙ መሆኑን ያሳያል ሲሉ አንድ የፍርድ ቤቱን ሂደት ለመከታተል የተገኙ ሰው ለኢሳት ዘጋቢ መግለጻቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

## ወያኔ በመላው አገሪቱ የፍርሃት ድባብ ለማስፈን . . . (ከገፅ 2 የዞረ)

አልፈጸምኩም...' ሲል ፍርድ ቤቱ በመሐል ገብቶ ዛሬ ሌላ ነገር ለመስማት ዝግጁ አይደለሁም፣ አሁን መናገር የምትችሉት ወንጀሉን ፈጽማችኋል ወይስ አልፈጸማችሁም በቃ! ሲል አቶ አንዷለም "ይገርማል እኔ ከዚህ በፊትም ፍርድ ቤት ቀርቤ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ይህ ፍርድ ቤት ለእኛ ፍትህ ለመስጠት የቆመ አያስመስለውም፤ የገጠመንን ኢፍትሃዊነት በተናገርን ቁጥር በጽሑፍ አቅርቡ እየተባልን አድማጭ አጥተን እንገላታለን፣ መንግሥት እኛን በእሥር ላይ አድርጎ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን አኬልዳማ በሚል በሦስት ክፍል ፕሮግራም የሥም ማጥፋት ዘመቻ እያካሄደብን ይገኛል፡፡' ብሏል።

ሁለተኛ ተከሳሽ የሆነው የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል ናትናኤል መኮንን "በሠላማዊ መንገድ መታገል ወንጀል ከሆነ አዎን ፈጽሜያለሁ፣ እንጂ የተባለውን የመንግሥት ድርሰት ግን አልፈጸምኩም በማለት የአላማ ጽናቱን አስመስክሮአል።

በትናትናው የወያኔ ፍርድቤት ውሎ ተከሳሾች የሰጡት ቃል በህብረተሰቡ ውስጥ ሲሰራጭ የወያኔን ማፈሪያነት ይበልጥ ይመሰክራል ህዝቡንም በ እልህ ለትግሉ ያነሳሳል ተብሎአል።

## በጀርመን የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በፋሽስቱ መለስ ዜናዊ

. . . (ከገፅ 2 የዞረ)

ይህ በዚህ እንዳለ፣ በዴንቨር ኮለራዶ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የወያኔ ባለስልጣናት ለአባይ ግድብ ማሰሪያ ቦንድ ለመሸጥና አዲሱን የዲያስፖራ ፖሊሲ ለማስተዋወቅ ላለፈው እሁድ ጠርተውት የነበሩት ስብሰባ እንዳይሳካ ማድረጋቸውን ከስፍራው የተላከልን ዜና ገለጸ።

በወያኔ አምባሳደር ተበጀ በርሄ የተመራው የልኡካን ቡድን ያቀደውን ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ሳይፈጽም፣ በአካባቢው በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በደረሰበት ተቃውሞ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ መመለሱን የገለጸው ዘጋቢያችን፤ የወያኔን ተላላኪዎች ለማሰባሰብ እቦታው ድረስ ተጉዞ የነበረው ተበጀ በርሄ ስበሰባው የህዝብ ስብሰባ እንዳልሆነ በማስታወቅ በስፍራው የነበሩት ተቃዋሚዎች አካባቢውን ለቀው እንዲሄዱ ለፖሊስ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ኢትዮጵያውያኑ ግን ተቃውሞአቸውን በመቀጠላቸው ስብሰባው ያለውጤት ለመበተን ችሎአል።

በሰሜን አመሪካ የሚኖሩ ኢትይጵያዊያን የፋሽስቱ ወያኔ ተላላኪዎች በስደት የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ለመከፋፈል የተሸረበውን ተንኮል በመከታተል እያከሸፉ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሎአል።

## ባለፈው እሁድ የተካሄደው የዘንድሮው ታላቁ ሩጫ

. . . (ከገፅ 2 የዞረ)

በዜማ እየታጀበ በዕለቱ ከተስተጋቡ መፈክሮች ጥቂቶቹ ኢህ አደግ ሌባ!!!!!፤ መንግሥት ሌባ!!!!!፤ ለዛሬ አመት አሃሃ ለዛሬ አመት በአዲስ መንግሥት!!!!! ምን አለ እስክንድር ምን አለ? ሀገሬን ተቼ ሀገሬን ትቼ አልሄድም አለ፤ ምን አለ ተመስጌን ምን አለ? ሀገሬን ትቼ አሃሃ አገሬን ትቼ አልሰደድም አለ፤ መለስ በቃ!!!!! ወያኔ በቃ!!!!! ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ!!!፤ ፒስ ነው እያለ፤ መሬቱን ሸጠው፣ አይቀርም አንድ ቀን አይቀርም አንድ ቀን መለስ እንደጋዳፊ ሊሆን!!! ፍትህ ለኢትዮጵያ!!! ፍትህ ለኢትዮጵያ!!! ፈዴራል ፖሊሶች ካሉበት ሲደርሱ ደግሞ "ፌደራል፤ ውሻ ውሻ፤ ፌደራል ውሻ ውሻ፤ ይጩህ እንደ ውሻ፤ የሚል ነበር ተብሎአል። በየአመቱ የሚደረገውን የሩጫ ውድድር ዋና አዘጋጅ የነበረው ሃይሌ ገብረስላሰንም ለማሞካሸት እድሜ ለሃይሌ፤ ተነፈስን የሚሉ ድምጾችም ጎላብለው እንደመፈክሮቹ ሲደመጡ እንደነበር ዘጋቢያችን ገልጾአል።

የህዝብ ብሶት ማሰሚያ ሆኖ በዋለው ከትናትና በስቲያ እሁድ ሩጫ ላይ ለተስተጋቡት መፈክሮች ቀስቃሾች ናቸው የተባሉ በርካታ ሰዎች ወዲያው በፌዴራል ፖልሲ ተይዘው ወደአልታወቀ ስፍራ እንደተወሰዱ ተያይዞ የደሬሰን ዜና ያስረዳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org